# ፖሊሲ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ግብአቶች:** DIE-RC, DJA, DJA-RA, ECF-RB, ECF-RC, EEA, EEA-RA, EEB-RA, ISB-RA, JPG, JPG-RA, KGA-RA

**ኃላፊነት ያለው ቢሮ:** Office of the Chief of District Operations

## ዘላቂነት

**A. ዓላማ**

የኃይል ቁጠባ እና ቀልጣፋ አጠቃቀምን ዘላቂ ተሞክሮዎች በሚመለከት የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የአካባቢ ጥበቃ ዘላቂ ተሞክሮዎች ማዕቀፍ እና የውሳኔ አሰጣጥ ቅድሚያ ትኩረት የሚሹ ነገሮችን አቅጣጫ ለማስቀመጥ

ተማሪዎች እና ሰራተኞች በሰው ልጅ የአካባቢ ለውጥ በግለሰብ እና በጋራ ጤና እና ደህንነት ላይ የሚያስከትለውን መዘዝ እንዲገነዘቡ እና በሁሉም ደረጃ የውሳኔ አሰጣጥን የአካባቢ ተፅእኖ እና ወጪዎችን እንዲያስቡ የሚያስችላቸው ውጤታማ የትምህርት እድሎችን ማሳደግ።

የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ጤንነት እና ደህንነት ለማበልጸግ በ MCPS ተቋማዊ አሠራር ስርአት ላይ በፍትሃዊነት የሚሰራጩ የአካባቢ ጥበቃ ዘላቂ ተሞክሮ የሚጠበቅበትን ሁኔታ ለማስቀመጥ

**B. ጉዳዩ**

ተማሪዎችን በመቀበል ደረጃ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሀገሪቱ ካሉት ከትላልቆቹ የት/ቤት ስርዓቶች አንዱ ሲሆን በሜሪላንድ ስቴት ውስጥ ትልቁ ነው። MCPS በግምት 500 ስኩዌር ማይል የሚያጠቃልል ከገጠር እስከ ከተማ የሚሸፍን ሲሆን ገባር ወንዞቹ ወደ ቼሰፒክ ቤይ ተፋሰስ የሚገቡትን ካውንቲ ያገለግላል። የትምህርት ተልእኳችንን ለመደገፍ በሚያስፈልጉት ፋሲሊቲዎች ብዛት ምክንያት፣ MCPS በካውንቲው ውስጥ ከፍተኛ የሃይል እና ሌሎች የተፈጥሮ ሪሶርሶችን ከሚጠቀሙት አንዱ ነው።

MCPS፣ በፍትሃዊ አጠቃቀም እና ቀስ በቀስ የአካባቢ ብክለት ተጽኖን እና ወጪዎቹን ከመቀነስ አኳያ ጤንነትን እና ደህንነትን የማሻሻል እና ውጤታማ የአካባቢ የአየር ንብረት ንፅህና ከመጠበቅ አንጻር ሆን ብሎ ዘላቂነት ያለው ትምህርት መስጠት አለበት።

ለዘላቂነት እና ለአካባቢ ጥበቃ የሚደረግ አጠቃላይ አቀራረብ በሰው-ተኮር የአካባቢ ለውጥ መዘዝ እና የተፈጥሮ አካባቢን ብክለት የሚከላከሉ፣ የሚደግፉ እና የሚታደሱ የአካባቢ እርምጃዎችን አስፈላጊነት እውቅና ይሰጣል። የአየር ንብረት ለውጥን መገንዘብ፣ ብክለትን ማስወገድ እና የአየር ንብረት ለውጥን ተፅእኖን የሚቀንሱ ኢንቨስትመንቶችን ቅድሚያ በመስጠት የህዝብን ሀብት በኃላፊነት የመጠቀም አሰራር ፅናት ይጠይቃል።

ዘላቂ የአካባቢ ጥበቃ አሻራ ቁልፍ ነገር ከባቢ የአየር ንብረትን ከብክለት ለመጠበቅ እና የኃይል ወጪዎችን ለመቀነስ በተቻለ መጠን የግሪንሀውስ ጋዝ (GHG) ልቀትን መቀነስ ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ከፌዴራል፣ ከስቴት እና ከአካባቢው አጋሮች ጋር በመተባበር የአካባቢን ትምህርት ቤት ማህበረሰቦች በሁለገብ ጥረቶች ላይ ንቁ ተሳትፎን ይፈልጋል፣ ክልላዊ (ሪጅናል) ችግሮችን ለመፍታት እና ምቹ የትምህርት አካባቢዎችን እና አስፈላጊ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና ተግባራትን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በፍትሃዊነት የሚተገበሩ የዘላቂነት ልምዶች እና ቴክኖሎጂዎች ያስፈልጋሉ።

C. *ሁኔታ*

1. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በጤና፣ እና ደህንነት ላይ በአየር ንብረት ብክለት ምክንያት የሚፈጠር ተጽእኖን ለመቅረፍ እና የበለጠ ጉልበት ቆጣቢ እና ወጪ ቆጣቢ የት/ቤት ስራዎችን ለማሳካት በፍትሃዊ እና ስልታዊ የሃብት መዘርጋት ላይ በመመስረት ስለ ዘላቂነት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ያካትታል። GHG ልቀትን በ 2027 ሰማንያ ፐርሰንት (80 በመቶ) እና በ 2035 መቶ በመቶ (100 በመቶ) ለመቀነስ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ያለውን ግብ ለማሳካት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ይደግፋል እና ንቁ ተሳታፊ ይሆናል።

2. ቦርዱ ለፈጠራዎች እና ስርአት አቀፍ ዘላቂነትን ለማሳካት ቁርጠኛ ነው-

   a) ከ GHG መፈጠር የሚደርስ ብክለትን መቀነስ፣

   b) ስርዓተ-አቀፍ ከፍተኛ የኢነርጂ አጠቃቀምን መቀነስ[1] ታዳሽ ባልሆኑ ሪሶርሶች ላይ መተማመን እና

   c) የፀሐይ ኃይል ማመንጨትን መጨመር እና ሌሎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን መጠቀም፣

   መ) የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎችን ለመቋቋም አስፈላጊ የሆኑትን ሪሶርሶች እና መሠረተ ልማቶችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚያስታጥቁ ስልቶችን መለየት፤

   e) ከግዢ ጋር በተያያዙ ውሳኔዎች፣ በኃይል አጠቃቀም፣ በትራንስፖርት፣ በምግብ አገልግሎት እና በሌሎች ተግባራዊ ነገሮችን ጨምሮ፣ የቆሻሻ ቅነሳን እና GHG ልቀቶችን እንደ መስፈርት መጠቀም፣ እና

   f) በሕንፃዎች ውስጥ-የነዋሪዎችን ጤና ለመጠበቅ እና የሕንፃዎች-አጠቃቀን ሥርዓት አፈፃፀም ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር የ MCPS ን ስራዎች እና የት/ቤት አካባቢዎችን ጥራት ማሻሻል።

3. MCPS የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ያከብራል፣ ሁለገብ የአካባቢ ጥበቃ ሊተርሲ ፕሮግራም፣ በወቅታዊ ስርአተ ትምህርት አቅርቦቶች ውስጥ እና ከሜሪላንድ የአካባቢ ጥበቃ ሊተርሲ ጋር በማጣጣም የተማሪዎችን እውቀት ለማዳበር እና ለመተግበር የአካባቢ ምህዳሮችን እንዲመራመሩ እድሎችን ይሰጣል። የተፈጥሮ አካባቢን ብክለት የሚከላከሉ፣ የሚደግፉ እና የሚታደሱ እና የሰው ልጅ እንቅስቃሴን አካባቢያዊ ተፅእኖ የሚረዱ እርምጃዎች፣ የአካባቢ ለውጥ ውጤቶች፣ እና የግለሰብ፣ የጋራ እና ማህበረሰባዊ የአካባቢ ለውጥ ምላሾችን ይንከባከባል።

D. **የሚፈለጉ ውጤቶች**

1. ሁሉም ተማሪዎች ወደፊት የበለፀገ አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ለማዘጋጀት ከዋናው የትምህርት ዓላማ ጋር በማጣመር፣ MCPS የተማሪዎችን ህይወት ለሚነኩ የአሁን/ወቅታዊ ውሳኔዎች ዘላቂነት ቅድሚያ ይሰጣል።

2. MCPS የአካባቢ ብክለት ተፅእኖን እና የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ይቀንሳል።

---

1 ይህ ፖሊሲ በፀደቀበት ጊዜ MCPS ስለ ኃይል አጠቃቀም በጣም የቅርብ ጊዜ የተሟላ መረጃ ያለው ከ 2019-2020 በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ተቋሙ ከመዘጋቱ በፊት ነው። 2019-2020፣ የትምህርት ስርዓት የኢነርጂ አጠቃቀም መጠን (EUI) 55.4 ሺህ ብሪቲሽ የሙቀት መለኪያ ዩኒት በአንድ ካሬ ጫማ (kBtu/sf) ነበር። ከታሪክ አኳያ፣ MCPS በ 2018–2019 የ 55.5 kBtu/sf፣ እና ከ 2017–2018 57.1 kBtu/sf ነበር።

3. በ MCPS አሠራር ተሞክሮ የትምህርት ስርአቱን አፋጣኝ ፍላጎቶች የአሁኑ እና የወደፊቱ ትውልድ ለችግር ወይም ለማንኛውም ሸክም ሳይዳረግ ያሚላል።

4. ሰራተኞች እና ተማሪዎች በሰዎች ምክንያት የሚመጣ የአካባቢ ለውጥ የሚያስከትለውን መዘዝ እና የግለሰብ፣የጋራ እና ማህበረሰባዊ የአካባቢ ለውጥ ምላሾችን ጠንቅቀው ያውቃሉ።

5. ሰራተኞች እና ተማሪዎች በሁሉም ደረጃዎች የውሳኔ አሰጣጥን የአካባቢ ተፅእኖ እና ወጪዎች ግምት ውስጥ ያስገባሉ።

6. MCPS ጤናማ እና ምቹ የመማሪያ አካባቢዎችን ይፈጥራል እና ይጠብቃል ይህም ከፍተኛውን የኢነርጂ ቁጠባና ቅልጥፍና ያስገኛል፣ በዘላቂነት ላይ የማያቋርጥ ትኩረት ይሰጣል።

7. MCPS ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ክላይሜት አክሽን ፕላን (Montgomery County Climate Action Plan) GHG ቅነሳ ኢላማዎች ጋር የሚጣጣሙ GHG እና አካባቢን የሚበክል ቆሻሻ ቅነሳዎችን የአሰራር ልምምዶች እና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል።

8. MCPS ትርጉም ያለው፣ የፀናእና ቀጣይነት ያለው የትምህርት ተቋማት ፖርትፎሊዮ ለመከወን ዕድሜ፣ የቦታ ሁኔታዎችን እና የጂኦግራፊያዊ ስርጭት ልዩነቶችን ያገናዘበ ውስን የገንዘብ ድጋፍን ያመቻቻል።

E. **ተግባራዊ ስልቶች**

1. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካዩ የሚከተሉትን ተግባራት የሚያካትቱ በሁሉም ት/ቤቶች ያልተበከለ የአካባቢን ዘላቂነት የማሳደግና የመጠበቅ ሂደቶችን ያፀናል እና ያጠናክራል።

    ሀ) ስርዓታዊ የአየር ንብረት መፍትሄዎችን ተግባራዊ ለማድረግ በዲፓርትመንቶች እና በአካባቢ ትምህርት ቤቶች ደረጃ ፈጠራን፣ ትብብርን እና አዳዲስ ግኝቶችን የሚያበረታታ ድርጅታዊ ባህል እና የአሰራር ሂደቶችን ለመመስረት እና ለማዳበር የአፈጻፀም ሂደቶችን ያዘጋጃል።

    b) ተማሪዎች እና ሰራተኞች በሰዎች የአጠቃቀም ጉድለት ምክንያት ለተፈጠሩ የአካባቢ ብክለት ለውጦች የግለሰብ፣ የጋራ እና የህብረተሰብ ምላሾችን እንዲረዱ ለማስቻል ዘላቂነት ያላቸው ጽንሰ-ሀሳቦችን በስርአተ ትምህርቶች እና ሙያዊ ትምህርቶች ውስጥ ያስገባል።

    c) ለአየር ንብረት መፍትሄዎች፣ የቅድመ ዝግጅት/የመላመድ ምላሾች እና ለአካባቢ ጥበቃ ዘላቂ ልምምዶች አስተዋፅዖ በሚያበረክቱ ተግባራት ላይ ለተማሪዎች እና ሰራተኞች እድሎችን ይሰጣል እና ተዛማጅ የስራ መንገዶችን ይዳስሳል።

2. የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ GHG ማመንጨትን እና ታዳሽ ያልሆኑ ሪሶርሶችን ፍጆታ ለመቀነስ እና ቅልጥፍናን ለመጨመር በአጭር እና በረዥም ጊዜ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ይለያል፣ ይህም የሚከተሉትን የሚያካትት ሲሆን ነገር ግን በዚህ ብቻ አይወሰንም።

    a) ነዋሪዎችን እና ኃላፊነት የሚሰማቸው የኦፕሬሽን ባለሙያዎችን በማሳተፍና በማበረታታት ሊታዩ እና ለመቆጣጠር የሚያመቹ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የኃይል እና የውሃ ፍጆታን በንቃት መቆጣጠር።

    b) ለፍጆታ የጅምላ ግዥ የሚመራ ዘዴን በመጠቀም ከፌዴራል፣ ከስቴት እና ከአከባቢ መስተዳድር ኤጀንሲዎች ጋር በተቀናጀ ጥረት ተገቢ የንብረት አያያዝና ጥበቃ ዕቅዶችን ለመዘርጋት መሳተፍ።

c) በሜሪላንድ አረንጓዴነታቸው የተረጋገጠ ትምህርት ቤቶችን እና ሌሎች ፕሮግራሞችን ለመደገፍ እና ለማስፋፋት ጠቃሚ ስልቶችን በአካባቢ ትምህርት ቤቶች ባህሪ ላይ የተመሰረቱ ዘላቂ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት እና መተግበር።

d) እንደአግባቡ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በናፍታ እና በቤንዚን የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን በኤሌትሪክ፣ ሀይብሪድ ወይም ሌላ ውጤታማ ወይም የንፁህ ነዳጅ ተጠቃሚ ተሽከርካሪዎችን ይተካል።

e) በትምህርት ተቋሙ ውስጥ የተመጣጠነ መገልገያዎችን እና የመሠረተ ልማት ፖርትፎሊዮዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የፀሐይ ኃይል የማመንጨት አቅምን ከፍ ለማድረግ እና የኃይል አጠቃቀምን መጠን ለመቀነስ እያንዳንዱን የግንባታ ፕሮጀክት በመንደፍ አዳዲስ እና ነባር ሕንፃዎችን የበለጠ ዘላቂ እና የአካባቢ ብክለትን ተከላካይ ለማድረግ የተነደፉ ስልቶችን እና ማሻሻያዎችን እናዳብራለን።

f) የመንግስት-የግል አጋርነትን እና የሚገኙ ዕርዳታዎችን እንዲሁም የታክስ ክሬዲቶችን በመጠቀም በነባር ሕንፃዎች ውስጥ ኃይል ቆጣቢ የመሠረተ ልማት ማሻሻያ ፕሮጀክቶችን እናካሄዳለን።

g) በተቻለ መጠን፣ ጠጣር ዕድገትን፣ የሕዝብ መሠረተ ልማትን በውጤታማነት ለመጠቀም፣ እና ከሕዝብ አገልግሎቶች ጋር ያለውን ቅርርብ ለማመቻቸት ትምህርት ቤቶችን ለጋራ አጠቃቀም የሚሰባሰቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

h) በፅናት የመቋቋም እና የግንዛቤ ችግሮችን ለመፍታት ሌሎች እርምጃዎችን መተግበር፣ ለምሳሌ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረቶች ላይ በዛፍ የተሸፈኑ እና ከቤት ውጭ የትምህርት ቦታዎችን መጨመር እና የዝናብ ውሃ ፍሰትን መቀነስ።

i) በ MCPS የግዥ መመሪያዎች ላይ ዝቅተኛውን መስፈርት መመስረት ከ-

(a) በአካባቢ የሚመረቱ ምርቶች፣

(b) ከፍተኛ የቆሻሻ/የብክለት መጠን ቅነሳ፣ እና

(c) በሁሉም የሥራ አካባቢዎች እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ምርቶች በሚገኙበት ቦታ፣ በልክ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ፣ በሁሉም የስራ ዘርፎች መጠቀም።

F. *ግምገማ እና ሪፖርት*

1. MCPS ከአካባቢ የሪፖርት ማቅረቢያ መስፈርቶች ጋር የተጣጣሙ ወቅታዊ አሠራሮችን በመጠቀም GHG ልቀቶችን ከምንጭ ለተቋሞቹ በየጊዜው ያስገነዝባል።

2. MCPS ከሁሉም የፌዴራል፣ የስቴት እና የአካባቢ መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ ግቦችን፣ አላማዎችን እና ዘላቂ ጥረቶችን የሚዘረዝሩ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያዘጋጃል።

3. ቦርዱ በግንባታ ፕሮጀክት ማሻሻያዎች ላይ ስለ ዘላቂነት ሁኔታ መረጃ ይቀበላል፣ እና የ MCPS ፋሲሊቲ ፖርትፎሊዮ ዘላቂ ባህሪያትን ለህዝብ ለማጋራት ድረ ገጾች እና/ወይም የአካባቢ ምልክቶችን የመሣሰሉ ዘዴዎችን ይጠቀማል።

4. ይህ ፖሊሲ እና ተዛማጅ ሰነዶች ከፌዴራል፣ ከስቴት እና ከአካባቢ መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ እየተሻሻለ ለባለድርሻ አካላት ይጋራል።

5. ይህ ፖሊሲ በቦርዱ የፖሊሲ ግምገማ ሂደት መሰረት ቀጣይነት ባለው መልኩ ይገመገማል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡*** የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀጽ፣ §75-312.1፣ የትምህርት ዲስትሪክት ኢነርጂ ፖሊሲዎች; የተብራራ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-117፣ በስቴት ውስጥ አረንጓዴ ትምህርት ቤቶችን ቁጥር መጨመር; የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ፣ 13A.04.17.01፣ የአካባቢ ሊተርሲ ፕሮግራሞች ከቅድመ መዋዕለ ሕፃናት–12፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ አፈፃጸም ደንብ 15-1፡ ደረቅ ቆሻሻ እና እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የአየር ንብረት የድርጊት መርሃ ግብር 2021፤ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ (2020–2029) 10 ዓመት የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እቅድ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ስራ አስፈፃሚ ደንብ 12-20 የ 2018 የአለም አቀፍ አረንጓዴ ከባቢ ግንባታ ኮድ ማፅደቂያ።

***የዚህ ፖሊሲ ታሪክ፡-*** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 654-73፣ ኖቬምበር 13/1973 የተሻሻለበት ውሳኔ ቁ. 285-97፣ ሜይ 13 ቀን 1997 ዓ.ም. ኤፕሪል 19 ቀን 2002 ገምግሟል። በውሳኔ ቁጥር የተሻሻለው 323-22፣ ጁን 28፣ 2022

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ጁን 2022